# <u>ልመኝ ! አዲስ ዓመት ሲለወጥ</u>

(ከበላይ መታፈሪያ)

አዲስ ዓመት ለሁላችን
መልካም አውደ ዓመት ለኢትዮጵያ አገራችን
ለመላው ሕዝብ ፍቅር፣ ተደላ ይሁን አለኝታ
የአንድነት፣ የሰላሙን ብልጽግና በደስታ።

> አሮጌው በአዲሱ ይቀየር ይለፋ
> ይሁን ዘመን ዓመቱ የኛ ተስፋ
> ያለፈው አልፎ ዓመት መራሬ
> ያስገኝልን መጪ ዓመቱ መልካሙን ፍሬ
> ኢትዮጵያዊ ወግ፣ወጌ፣ ድፍረትን
> ለእናት አገር፣ ኢትዮጵያዊ ቃል ኪዳን
> ትውልድ ታሪክን አስታወሰንና አስበን
> እንድንሠራ ጠቃሚውን መልካሙን
> የአንድነት፣ኅብረቱ መካተት
> ሁሉ እንዲሆን የአገሩ ባለቤት
> እንድናይ ነው የሁሉም መብት የዜግነቱን ኩራት

የቅርሳችን አካል ዘመን መቁጠሪያን
ተመርኩዘን እናክብር ዓመታትን
አለን ሞራል ለዚህ ብቃት
የራሳችን ቁጥር ግኝት
የሚያኮራ ነው ለትውልድ ለዘመናት
ልዩ እሚያደርገን ከሌሎች ሁሉ አሐዱነት
ፍልስፍናው ለኛ ብቻ በልዩነት
ያክብረው! ሃቀኛ ኢትዮጵያዊ  በደስታ በኩራት።

> አዲስ ዓመት እናክብር ሲደመጥ
> እያንዳንዳችን ማጤን፣ ያለብን በርግጥ
> በወል መጠየቅ ያለብንም ጉዳዮች
> ዛሬ ያለንበት የጭቆና ዓመቶች
> በወያኔ የግፍ አገዛዝ የፈሰሰው ደም

ይሁን እየታሰበ በሕዝባችን ያለው ረሃብ በሽታውም
በችግር የተቆላው፣ የታሰረው፣ በስደት ያለውንም

ዓመት ሄዶ ዓመት ሲለወጥ
ነው ዓመት  በምኞት፣ በተግባርም ለውጥ የሚሰጥ
ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ
ነው ዓመት ጥሩ ነገር ሊያሳካ
ዘመን አዲስ ዓመት ሲሄድና ሲመጣ
እየተመኘን መጥፎ ችግር እንዲወጣ

ሰላም ብልጽግናን እየተመኘን
መልካም ጥሩ ነገር እንዲኖረን
ለደስታ ነው ለትንሳኤ ምኞታችን
ዓመት በዓመት ሲተካ ሲቀየር
ለመስራት ነው አጠንክሮ በምር።

ዓመታት ምዕት ዓመታት ሲሄዱና ሲመጡ
ዓመት በዓመት ሲያልፉና ሲለወጡ
ጊዜ ቆጥሮ ዓመት ሲሄድ
ዓመት፣ ወር፣ ቀን፣ ሰዓት፣ ሰኮንድ
ቆጥረን ቆጣጥረን አዲሱ ይምጣ ያለፈው ይሂድ
ያለምነው ይሁን የፈለግነውን እንስራበት
ለአገር፣ ታሪክ ትውልድ ግኝት ነፃነት ኩራት።

አዲስ ዓመት እንዲሆን ለኛ
ለአገር ወገን የደስታ መገኛ
ከአለፈው መማር መልካሙን መጠበቅ
የመጡበትን ያሉበትን ይዞታ ማወቅ
መጭውን ከዛሬው አጢኖ በመረዳት
መተለምና መወጠን ያሻል፣ ይገባል በጊዜዓት።

ከአሮጌው በአዲሱ ጥሩ ነገር እንድናገኝ
በጊዜው እንጠቀም ጥሩውንም እንመኝ
መልካሙ እንዲቆይ እንዲጠበቅ
መጥፎ እኩዬ ይነቀል ዛሬ እንላቀቅ
በዘመናት እንጠቀም እንወቅ።
ይሁን መጥፎው መወገዱ
ተገቢ ነው ጥረት በየትውልዱ

ጥሩ አስበን ካልሰራን
መልካም እንድንሆን ካልጣርን
ምንድነው አዲስ ዘመን
የማንሰራ የማናገኝ ከሆነ ጥሩውን !

ጊዜን ዓመትን ካልሰሩበት፣
የተሻለ ኑሮ ሕይወት ካላዩበት፣
ምንድነው ዓመት የዘመናት መሄድ መምጣት
ካልተገኘበት ነፃነት ታሪክ ኩራት።

ካልሰሩበት ትውልድን የሚያኮሩ
ምንድነው ቀናት ዓመታትን ማስቆጠሩ
አውደ ዓመት መጣ እያሉ መደሰቱ
አዝነው፣ አጥተው በከንቱ
ለምን ይሆን አዲስ ዓመት ማለቱ
ከዘንድሮው ካልተሻለ መጭ ዓመቱ

እንለውጥ ዓመቱን በአንድነት በጋራ፣
እንዲሆንልን የደስታ ብልጽግና የሚያኮራ፣
ዓመት ሄዶ ዓመት ቆጥሮ፣
ተድላ መጥቶ በጊዜውም በቀጠሮ፣
ሁሉም ሲያልፉ እሮሮ ቀርቶ፣
የተመኙት ያለሙትን አግኝቶ፣
በአገራችን በኢትዮጵያ ሁሉ መጥፎ አልቆ አብቅቶ፣
ስንኖር ነው ጠንክሮ በአንድነት ጸንቶ ሰርቶ፣

ዓመት አዲስ ዓመትን የምናከብር፣
ኢትዮጵያን አስከብረን ዳር ድንበር፣
ስንኖር ፣ ስንሆን ነው እንደ ጥንቱ በክብር።

ፈጣሪያችን ዕርቅ ሰላም አውርዶ
መጥፎ ሰይጣንን አስወግዶ
ወገን፣ አገር የከዳውን አዋርዶ
የአምላክ ቸርነት ለኢትዮጵያ ተፈቅዶ
አንደበቱ የረጋ፣ በጥበብ የተሞላ አዋቂውን
ታዛዥ ለሕዝብ አሳቢውን አገልጋዩን
ጥሩ መሪ ለአገራችን ለኢትዮጵያ ይለግሰን
እኛም እንጸልይ ከልብ በርጋታ አዘወትረን
እናመስግን ፈጣሪን ይፍቀድ ይባርከን።